Oromia INSURANCE

## ኦሮሚያ ኢንሹራንስ (አ.ማ.)
## ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ጥቆማ ለመቀበል
## የወጣ ማስታወቂያ

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መምሪያ ቁጥር SIB/48/2019 አንቀጽ 6.1.4 መሠረት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የተሰየመው የኦሮሚያ ኢንሹራንስ (አ.ማ.) የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ሥራውን የጀመረ በመሆኑ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ህጋዊ መስፈርቶች የሚያሟሉ የዕጩ ዳይሬክተሮች ጥቆማን ከኩባንያው ባለአክሲዮኖች ከሰኔ 24 ቀን 2018 እስከ መስከረም 19 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ ይቀበላል::

**ለቦርድ አባልነት በዕጩነት ለመጠቆም የሚያበቁ መስፈርቶች:-**

1. የኩባንያው ባለአክሲዮን የሆነ/የሆነች፣ ቢመረጥ/ብትመረጥ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ/ች እና እድሜው/ዋ 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤
2. የትምህርት ደረጃ፣ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ከታወቀ የትምህርት ተቋም ያላቸው፤
3. የሥራ ልምድ:- 5 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜ በቢዝነስ ማናጅመንት፣ በተለይ በኢንሹራንስ ቢዝነስ ልምድ ያለው/ያላት እና/ወይም፣ በኢንሹራንስ፣ በሪስክ ማኔጅመንት፣ በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ ማናጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በኦዲቲ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት እና ሰስቴንቢሊቲ በቂ ልምድ ያለው/ያላት ቢሆኑ ይመረጣል::
4. የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ያልሆነ/ች፤
5. የኦሮሚያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ሰራተኛ ያልሆነ/ች፤
6. በሌላ የፋይናንስ ተቋም የቦርድ አባል ያልሆነ/ች፤
7. የህግ ሰውነት ያለው ድርጅት በዕጩነት ሊጠቆም ይችላል፤ሆኖም በጥቆማው ወቅት ድርጅቱን የሚወክልና እዚህ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ/የምታሟላ የተፈጥሮ ሰው ማሳወቅ አለበት፤
8. በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ተግባር ያልፈፀመ/ች፣ ለፋይናንሻል ተቋማትና ለተቆጣጣሪ አካል ሐሰተኛ መረጃ ያልሰጠ/ች፤ የሥነ-ምግባር ደንቦችን ባለማክበር የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ያልተወሰደበት/ባት፤ በሙስና ወንጀል ተከሶ/ሳ ያልተፈረደበት/ባት
9. ከመምረጥና መመረጥ መብት ያልተገደበ/ች፤
10. የፋይናንሻል ጤናማነትን (Financial Soundness) መስፈርት የሚያሟላ፤ ማለትም በኪሳራ ላይ ያልሆነ/ች፣ የታክስና የባንክ ግዴታዎቹን የተወጣ/ች::
11. ከሚጠቆሙ ዕጩዎች 1/3ኛዎቹ የሚጠቆሙት ከኩባንያው ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል 2 ከመቶ በታች ባላቸው (ተጽዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ) ባለአክሲዮኖች ብቻ ሲሆን ቀሪ 2/3ኛዎቹ በሁሉም ባለ አክስዮኖች ይጠቆማሉ::
12. ከላይ የተጠቀሱት መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባልነት የሚጠቆም ማንኛውም ባለአክሲዮን በብሔራዊ ባንክ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ እምነት የሚጣልበት/ባት፣ የኩባንያውን ዓላማዎች ለማሳካት በጎ ራዕይ ያለው/ያላት፣ ለመሥራት ፈቃደኛ እና ቁርጠኛ የሆነ/የሆነች፣ በጋራ አሰራር ሂደት ውስጥ ታማኝ፣ ሐቀኛ፣ የተሟላ ስብዕና ያለው/ያላት መሆን አለበት/ባት::

ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የኩባንያው ባለአክሲዮን የሆናችሁ ከላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩዎችን ለመጠቆም የተዘጋጀውን ቅጽ ከኩባንያው ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ቢሮ ወይም በአቅራቢያዎ ካሉ የኢንሹራንስ ኩባንያው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመውሰድ ወይም ከኩባንያው ድህረ-ገፅ https://oromiainsurance.com/ በማውረድ ከኩባንያው ዋና መ/ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ በሚከተሉት መንገዶች ጥቆማ እንድታቀርቡ ተጋብዛችኋል::

1. ኦሮሚያ ኢንሹራንስ ዋና መ/ቤት (ወሎ ሰፈር ኢትዮ ቻይና መንገድ፤ ሲድያ አስናቀ ህንጻ) 1ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ቢሮ፤ ወይም
2. በአቅራቢያዎ ባሉ የኢንሹራንስ ኩባንያው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአካል በማስረከብ፤ ወይም
3. በአስመራጭ ኮሚቴው ኢሜይል አድራሻ፡ oicboardelection@oromiainsurance.com ላይ በመላክ ጥቆማውን መስጠት ይቻላል::

**ማሳሰቢያ፤**

1. ከላይ በተዘረዘሩት ሶስቱም አማራጮች የሚላክ የጥቆማ ቅፅ፣ በትክክል ተሞልቶ በጠቋሚው ባለአክስዮን መፈረም ይኖርበታል፤ ጠቋሚው ባለአክስዮን ድርጅት ከሆነ፣ በሁሉም የጥቆማው ቅጽ ገፆች ላይ የድርጅቱ ማህተም መመታት አለበት:: በኢሜይል የሚላክ ጥቆማ ተቀባይነት የሚኖረው በጠቋሚው ባለአክሲዮን ኢሜይል አድራሻ ከተላከ ብቻ ነው::
2. ጠቋሚ ባለአክስዮኖች የሞሉትን የጥቆማ ቅፆች፣ በኩባንያው ዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአካል የሚያስረክቡ ከሆነ፣ እራሳቸው በአካል በመገኘት እና ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየት ወይም በህጋዊ ወኪላቸው አማካይነት ማስረከብ አለባቸው::
3. ከላይ በተ.ቁ 1 እና 2 በተገለፁት ሁኔታዎች ያልተላኩ የጥቆማ ቅፆች ተቀባይነት አይኖራቸውም::

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡ 0115589450 መደወል ይችላሉ::

**የኦሮሚያ ኢንሹራንስ (አ.ማ) የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ**